# የሳንባ ነቀርሳ

የታካሚው መረጃ ከስዊድን ተላላፊ በሽታ ሐኪም

## ይህንን መረጃ ለምን አገኙሁት?

ይህ መረጃ የደረስዎት፡ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ያለብዎት ወይም ይኖርብዎት ይሆናል ተብሎ ስለተጠረጠረ፥ ህክምና ማድረግ ስላስፈለግዎት ነው። ይህ ጽሑፍ ስለ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ፣ ከበሽታው እንዴት እንደሚድኑ እና እርስዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ የሚያስረዳ መረጃ ይዟል።

## ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?

ሳንባ ነቀርሳ (TBC ወይም TB) *"Mycobacterium tuberculosis"* በመባል በሚታወቀው የሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ የሚፈጠር የሰንባ ነቀርስ በሽታ ነው። የበሽታው ምልክቶች ብዙውን ጊዜ፥ በበሽታው ከተያዙ ከረጅም ጊዜ (ወራት ወይም ዓመታት) በኋላ ነው የሚታየው። በአብዛኛው ግዜ ባክቴሪያው የሳንባ ንዳድ ወይም መበከል የሚያመጣ ሲሆን፥ ሌሎች የሰውነት ክፍሎችን፣ ለምሳሌ እጢዎችን፣ የሳንባ ከረጢትን፣ አጽምን፣ አንጎልን እና ኩላሊትን ሁላ ይነካል።

## የሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይተላለፋል?

በሽታው በሳንባቸው ውስጥ የሳንባ ነቀርሳ ካለባቸው ሰዎች ይተላለፋል። አንድ ሳምባ ነቀርሳ ያለበት ሰው፥ ቤት ውስጥ ሲስል፣ ሌላው ሰው ያንን ዓየር ሲስብ ባክቴሪያ ያዘለ በጣም ጥቃቅን ጠብታዎችን ወደ ሳንባው ያስገባል። ነቀርሳ በዋናነት የሚተላለፈው ከበሽተኛው ጋር በሚደረግ የቅርበትና የረጅም ግዜ ግኑኝነት ነው። አንድ ሰው በአጭር ጊዜ ግንኙነት ወይም አልፎ አልፎ በሚደረጉ ግንኙነቶች በበሽታው የመጠቃቱ የተለመደ ነገር አይደለም።

## ሳንባ ነቀርሳ እንዳለብዎት በምን ይታወቃል?

የበሽታው ምልክቶቹ፡ የሳንባ ነቀርስ ባክቴሪያው በሰውነት ውስጥ በሚገኝበት ቦታ ላይ የተያያዘ ነው። በሰፊው የሚታወቅባቸው ምልክቶች፥ ረዘም ላለ ግዜ የሚቆይ (ሶስት ሳምንታት በላይ) የማሳል ሁኔታ፥ በሌሊት በላብ መዘፈቅ፥ ትኩሳት እና የክብደት መቀነስ ናቸው። ሌሎች የበሽታው ምልክቶች፥ እብጠት (የሊምፍ ኖዶች የሳንባ ነቀርሳ) ወይም ህመም (የአጥንት ወይም የሆድ ሳንባ ነቀርሳ) ሊያካትቱ ይችላሉ።

## ሳንባ ነቀሳ እንዴት ይተላለፋል?

የሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች፣ ባክቴሪያዎች በአክታ ውስጥ የሚገኙባቸው፣ ሕክምናው ከመጀመሩ በፊት በከፍተኛ ሁኔታ ተላላፊ ሊሆኑ ይችላሉ። የበሽታው የመተላለፍ አቅም፥ በመጀመሪያዎቹ የሕክምና ሳምንታት ውስጥ በፍጥነት እየቀነሰ ይሄዳል። ከሳንባ ውጭ የሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች በሽታውን አያስተላልፉም። ሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ትንንሽ ልጆች ከሞላ ጎደል በሽታውን ፈጽሞ ማስተላለፍ አይችሉም። ሳንባ ነቀርሳ በልብስና በሌሎች እቃዎች በኩል ሊተላለፍ አይችልም። በሽታው ከቤት ውጭ እምብዛም አይተላለፍም።

## ሳንባ ነቀርሳ አደገኛ ነውን?

ያልታከመ የሳንባ ነቀርሳ ወደ ከባድ ጉዳት ሊያመራ ይችላል እና አንዳንድ ጊዜ ለሕይወት አስጊ ሊሆን ይችላል። ትናንሽ ልጆች እና የተዳከመ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ያላቸው ሰዎች፥ በሳንባ ነቀርሳ ምክንያት በጠና የመታመም አደጋ ላይ ናቸው።

## ሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይድናል?

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ የሚፈወሰው በሽታውን የሚፈጥረው ባክቴሪያን የሚገድል መድሃኒት በመውሰድ ነው። ህክምናው ረጅም ግዜ የሚወስድ ሲሆን በብዙ ወራት ውስጥ የሚካሄድ ነው። ህክምናውን ሃኪም ባዘዘው መሠረት መውሰድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

ህክምናው በሚወሰዱበት ግዜ ከታዘዙት ክኒኖች ውስጥ ምንም መዝለል አይገባም። መድሃኒት አወሳደዱ በታዘዘው መሠረት ካልተከናወነ፥ ባክቴሪያው መድሃኒቱን የመለማመድና የመቋቋም አቅም ስለሚፈጥር፣ በመካያው በሽታውን ለመፈወስ አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠራል።

የሳንባ ነቀርሳ መድሃኒት የሚሰጠው በነጻ ነው፣ የህክምና ክትትሉ እንዲሁ ነጻ ነው።

## ሌሎች ሰዎችን ላለመበከል ምን ማስታወስ አለብኝ?

በተላላፊ በሽታዎች ሕግ መሠረት፥ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በአጠቃላይ አደገኛ በሽታ ነው። ስለዚህ ሃኪምዎ የሚሰጥዎትን የስነ-ምግባር ደንቦች፥ በሚገባ መከተል ይኖርብዎታል። አሳዳጊዎች ልጆች የስነ-ምግባር ደንቦች እንዲከተሉ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

ሌሎችን ላለመበከል ለተወሰነ ጊዜ ሆስፒታል መተኛት ሊያስፈልግዎት ይችላል።

### የስነ-ምግባር ደንቦች

- ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ካለብዎት ወደ ሥራ፣ ትምህርት ቤት ወይም ወደ መዝናኛ እንቅስቃሴዎች መሄድ የለብዎትም።
- ዶክተርዎ ለቀጣይ ክትትል መምጣት እንዳለብዎት ከነገረዎት፥ እንደሱ ማድረግ ይኖርብዎታል።

**የስነ-ምግባር ደንቦች ለምን ያህል ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናሉ?**
ሐኪምዎ ተላላፊ እንዳልሆኑ እስኪናገር ድረስ፥ የስነ-ምግባር ደንቦች መከተል ይኖርብዎታል።

**የተሰጥዎት የስነ-ምግባር ደንቦች ስህተት ነው ብለው ካመኑ?**
በክልልዎ ውስጥ ያለው የተላላፊ በሽታ መቆጣጠሪያ ሐኪም፥ የተሰጠውን የስነ-ምግባር ደንቦች ውሳኔ እንዲገመግም መጠየቅ ይችላሉ። ከዚያም በክልልዎ ውስጥ ያለውን ተላላፊ በሽታ ሐኪም ያነጋግሩ።

[የተላላፊ በሽታ ቁጥጥር ሐኪሞች የመገኛ አድራሻ | የተላላፊ በሽታ ቁጥጥር ሐኪሞች ማኅበር (slf.se)]

እንዲሁም በክልልዎ ውስጥ ያለውን የጤና ማዕከል በመደወል፥ ከተላላፊ በሽታ ሐኪም ጋር መገናኘት ይችላሉ።

ውሳኔው የመገምገሙ ሂደት ከመጠናቀቁ በፊት ግን፣ የተሰጡዎትን ደንቦች መከተል አለብዎት።

## የኢንፌክሽን ምንጭ ክትትል

በኢንፌክሽን መቆጣጠሪያ ህግ መሰረት፣ በኢንፌክሽን ምንጭ ክትትል ውስጥ መሳተፍ አለብዎት። ይህ ማለት መቼ፣ የት እና እንዴት እንደተያዙ እና ሌሎችን እንደበከሉ ለማወቅ፥ ለጤና ባለሙያዎች መረጃ መስጠት አለብዎት ማለት ነው። የሚነግሯቸው ነገሮች ሚስጥራዊ (በሚስጥር የሚያዙ) ነው። የሳንባ ነቀርሳ ያለባቸውን ሰዎች ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው፥ እነሱም ህክምና ማግኘት ስላለባቸው። አንድ ሰው ሊተላልፍበት ይችላል፥ ነገር ግን በሕመም ላይታመም ይችላል።

## ተጨማሪ መረጃ

[Tuberkulos – tbc | 1177 (1177.se)]